3.1.0/48/07

07 መስከረም 2007

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority

ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች

**በያሉበት፤**

**ጉዳዩ:- <u>በግማሽ ቫን ተሽከርካሪዎች ላይ የተሰጠ የታሪፍ አመዳደብ ውሳኔ፡</u>**

በተለያዩ ጊዜያት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እና ሰዎችንና ዕቃዎችን ለማጓጓዝ የተሠሩ ግማሽ ቫን ተሽከርካሪዎች ዋና ተግባር የሰው ማጓጓዣ ነው ወይስ የዕቃ ማጓጓዣ ነው የሚለውን የታሪፍ አመዳደብ ጥያቄ አስመልክቶ በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች እና በአስመጪዎች መካከል የተነሳውን የታሪፍ አመዳደብ ክርክር ለመፍታት ከዋጋ ትመና እና ታሪፍ ምደባ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 3.1.0/930 ሰኔ 11 ቀን 2006 ዓ.ም. ለሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የተላለፈው ማብራሪያ የበርካታ አስመጪዎችን ቅሬታ አስነስቷል፡፡ አስመጪዎቹ ከዚህ በፊት ይሰራበት በነበረው ልማዳዊ አሠራር ታሪፉን በመመደብ አነስተኛ ቀረጥና ታክስ እየከፈሉ ሲያስገቡ በመቆየታቸው፣ አሁንም በዚሁ አሠራር መሠረት እንደሚሰራ በመገመት ከውጭ ግዢ በመፈጸም ያስገቡ መሆናቸውን በመግለጽ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ሐምሌ 28 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለዋ/መ/ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የባለሥልጣን መ/ቤቱ የበላይ አመራር መስከረም 3 ቀን 2007 ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ጉዳዩን ለማጣራት የተቋቋመው ኮሚቴ በአዲስ አባበ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እና በአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ባደረገው ዝርዝር አካላዊ ፍተሻ ላይ በመመስረት ባቀረበው የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡ የተቋቋመው ኮሚቴ ባደረገው ማጣራት ቅሬታ የቀረበባቸው ግማሽ ቫን ተሽከርካሪዎች የሚሰጡት ዋና አገልግሎት ሰዎችን ለማጓጓዝ መሆኑንና፣ ሹፌሩን ጨምሮ ከ10 (አስር) ሰው በታች የሚጭኑ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የአንዳንድ ግማሽ ቫን ተሽከርካሪዎች ከጋቢናው በስተጀርባ ያለው ክፍት ቦታ ወንበር ያልተገጠመላቸው ቢሆንም፣ ወንበር ሊገጠምላቸው እንደሚችል እና ሰዎች ሊጭኑ እንደሚችሉ አመላካች ሁኔታዎች መኖራቸውን አረጋጧል፡፡

በመሆኑም በሀርሞናይዝድ ሲስተም የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብ ደንብ እና የዕቃዎችን ታሪፍ አመዳደብ አስመልክቶ በዓለም ጉምሩክ ድርጅት በወጡ አግባብነት ያላቸው የሰነድ ማስረጃዎች መሠረት ቅሬታ የቀረበባቸውና ከነዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ግማሽ ቫን ተሽከርካሪዎች በታሪፍ አንቀጽ 8703 ሥር የሲሊንደር ይዘታቸውና የተገጠመላቸው የሞተር ዓይነት እየታየ በየሚመለከታቸው የታሪፍ ቁጥር ሊመደቡ እንደሚገባ ግንዛቤ በመውሰድ የበላይ አመራሩ ወስኗል፡፡

9/01/07

ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችና አስመጪዎች የታሪፍ አመዳደብ ሥርዓቱን በአግባቡ ካለመረዳት የተነሳ ተሽከርካሪዎቹን በተሳሳተ ታሪፍ እየመደቡ ሲያስገቡ የቆዩ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ፍትሐዊ አሠራርና መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አኳያ፣ ከሐምሌ 30/2006 ጀምሮ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የተጫኑ ማናቸውም ግማሽ ቫን ተሽከርካሪዎች የማስጫኛ ሰነዳቸው ቀን (Date of Bill of Loading) ወይም (Air way Bill) እየታየ በታሪፍ አንቀጽ 8703 ሥር የሲሊንደር ይዘታቸውንና የተገጠመላቸውን የሞተር ዓይነት በማገናዘብ በየሚመለከታቸው የታሪፍ ቁጥር እንዲመደቡ፤ ከላይ ከተጠቀሰው ቀን በፊት የተጫኑ ተሽከርካሪዎች ደግሞ በነበረው አሠራር እንዲፈጸም ስለተወሰነ በዚሁ መሠረት እንዲፈጸም እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ከይዳኪ ገዛኸኝ
ም/ዋና ዳይሬክተር
የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና
ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Revenues and Customs

ግልባጭ፡-

- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር
- ለሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ሥራዎች ዘርፍ
- ለአገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለዋጋ ትመና እና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
  የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ